
# 06

# ፆታዊ ጥቃት



## ጾታዊ ጥቃቶችን መከላከል

**ትምህርት እና ግንዛቤ፦** ጾታዊ ጥቃቶችን ለመከላከል ስለ ጾታዊ ጉዳይ ተጨባጭ ግንዛቤ እና ትምህርት አጠናክሮ ተገቢ መረጃዎችን፣ መገናኛ ወይም ግንኙነቶችን እና የመማሪያ ስልቶችን ስትራቴጂክ በሆነ መልኩ በመጠቀም ጾታዊ ጎጂ ልማዶች እና አስተሳሰቦች እምነቶች እና አባባሎችን መለወጥ

**ማህበረሰብን መቀስቀስ እና ማሰማራት፦** የማህበረሰብ ክፍሎችን እና አባላትን እንዲሁም የአካባቢው ሃገር ሽማግሌዎችን በመቀስቀስ፣ በማደራጀት እና ስለ ጾታዊ ጥቃቶች አስመልክቶ የተቀናጀ እርምጃ እንዲወስዱ ማድረግን ያካትታል።

**የህግ እና ፖሊሲ ማሻሻያዎች** በአግባቡ ጾታዊ ጥቃቶችን ለመከላከል እና የተሻለ ውጤት የሚያስገኙ የአስፈጻሚነት፣ አተገባበር እና የህግ ማዕቀፎችን፣ ደንቦችን እና ፖሊሲዎችን በየጊዜው ማሻሻል እና ተግባራዊ ማድረግ ያስፈልጋል።

**የምጣኔ ሃብት አቅም ማጎልበት** በተለይ የእያንዳንዱን ግለሰብ የምጣኔ ሃብት እና የገቢ ምንጭ በማሳደግ እና የውሳኔ ሰጪነት አቅም በማጎልበት በተለይ በሴቶች እና በተገለሉ ማህበረሰቦች ላይ ትኩረት አድርጎ መስራት ለጾታዊ ጥቃት ተጋላጭነታቸውን ይቀንሳል።

## የጾታዊ ጥቃት ስልታዊ ምላሾች

**በአንድ ማዕከል ዘርፈ ብዙ አገልግሎቶች አቅርቦት፦** ይህ አይነቱ አካሄድ የጾታዊ ጥቃት ሰለባ የሆኑ ወገኖች የሚያስፈልጋቸውን በርካታ መሰረታዊ አገልግሎቶች በአንድ የአገልግሎት መስጫ ማዕከል ማግኘት እንዲችሉ ማድረግ ነው።

**የጤና እንክብካቤ አገልግሎቶች፦** የሚያመለክቱት የጾታዊ ጥቃት ሰለባ ለሆኑት የደረሰባቸውን የድህረ ጥቃት ዘርፈ ብዙ ችግሮችን ለመቅረፍ የሚያስፈልጋቸውን አካላዊ፣ ስነ-ልቦናዊ ስሜታዊ እና የስነ ተዋልዶ ጤንነት አገልግሎቶች እንዲሁም ለአጭር ጊዜ እና ለረዥም ጊዜ የሚያገለግላቸው የህክምና እና የስነ ልቦና ህክምና አገልግሎት በሰለጠነ የጤና ባለሙያዎች መስጠትን ያካትታል።

**የህግ ድጋፍ፦** የሚያመለክተው ጾታዊ ጥቃት ለተፈጸመባቸው ወገኖች የሚያስፈልጉ የተለያዩ አገልግሎቶች እና የሚደረግላቸው ድጋፎች የሚያካትት ሲሆን እነዚህ ዘርፈ ድጋፎችን ግለሰቦቹ ስለ ህግ አገልግሎት እና ፍትህ ስርዓት ግንዛቤ እንዲኖራቸው እና እንዲያስሱ እንዲሁም ተደራሽ እንዲሆን የሚረዳ መደበኛ የድጋፍ አገልግሎት ነው።

**የመጠለያ እና ማህበራዊ ድጋፎች፦** ይህ አይነት አገልግሎት ጾታዊ ጥቃት ለደረሰባቸው የሚደረግ የመከላከያ የእንክብካቤ እና ተጨባጭ ድጋፎች እንዲሁም የስነ-ልቦና ወይም ስሜታዊ ድጋፎች ሲሆን እነዚህ ድጋፎችን በጥቃቱ ሰለባዎች ላይ ሊደርሱ የሚችሉ አፋጣኝ አደጋዎች ማምለጥ እንዲችሉ እና ለወደፊት የተረጋጋ ህይወት መምራት እንዲችሉ እንዲሁም ከደረሰባቸው ጥቃት የተነሳ የደረሰባቸውን የስነ ልቦና የስነልቦና ጉዳት/ጠባሳ እንዲፈወሱ እና ወደ ቀድሞ ኑሯቸው መመለስ እንዲችሉ የሚረዱ የድጋፍ አይነቶችን ያካተተ አገልግሎት ነው።

**የጉዳይ አያያዝ አቀራረቦች፦** በዚህ አቀራረብ የሰለጠኑ ባለሙያዎች እንደ ማህበራዊ ሰራተኞች ወይም የጉዳይ ሰራተኞች ከጾታዊ ጥቃት ሰለባ የነበሩ ሰዎችን ፍላጎት ይገመግማሉ፣ የግለሰብ እንክብካቤ እቅድ ያዘጋጃሉ እና የጤና፣ የስነ-ልቦና ድጋፍ፣ የደህንነት እቅድ፣ የህግ እርዳታ እና መጠለያን ጨምሮ የተለያዩ አገልግሎቶችን ማግኘትን ይጨምራል።